2015

ዴሞክራሲያዊነትን በኢትዮጵያ ለማስፈን

# የረጅሙ ጉዟችን

# ጅማሬ

CARD
የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR THE ADVANCEMENT
OF RIGHTS AND DEMOCRACY

MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF THE GAME!



የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY

MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF THE GAME!

## ስለ ካርድ

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ሴንተር ፎር አድቫንስመንት ኦፍ ራይትስ ኤንድ ዴሞክራሲ /ካርድ/) ቦርድ-መር፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ 113/2011 መሠረት፣ በመዝገብ ቁጥር 4307፣ ሐምሌ 17፣ 2011 ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ነው።

ካርድ በሰብዓዊ መብቶች እሴቶች ላይ የቆመ ዴሞክራሲያዊ ባሕል ያበበባት ኢትዮጵያን ማየት ራዕይ አድርጎ ሰንቆ፥ የኢትዮጵያ ዜጎች እና የዜጎች ማኅበራት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር በመሟገት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲያሰፍኑ የሚያስችላቸውን የአቅም ግንባታ ማድረግ ተልዕኮ በማንገብ እየሠራ የሚገኝ ድርጅት ነው።

**© የመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል፣ 2015**

## ለበለጠ መረጃ

ኢሜል: info@cardeth.org
ሶሻል ሚዲያ: @CardEthiopia
ድረ ገፅ: www.cardeth.org
ስልክ: +251 116 671 657

**የመፅሀፍ ዲዛይን: አርመን: armonimsolomon@gmail.com**

# ማውጫ


**ስለ ካርድ አጭር መግለጫ** 2

**የመረ ቃላችን ፅንሰ ሐሳብ** 3

**መርሓ ግብሮች** 4

1. የዜግነት ተሳትፎ ..... 5
2. የወጣቶች እና ሴቶች አቅም ማጎልበት ..... 6
3. የሚዲያ አረዳድ ክኅሎት ..... 7
4. የዲጂታል መብቶች ..... 8
5. የዴሞክራሲያዊነት ምዘና ..... 9

**ሥነ ዘዴያችን ከራዕያችን ያለው ዝምድና** 10

በመንገዳችን የሚያተጉን ተስፋዎች ..... 12

**የዜጎች በራሳቸው ጉዳይ ባለቤት መሆን** 12

**ስለ ሰላም መቆም** 15

**ተሟጋች ትውልድ ማፍራት** 16

**በአገር በቀል ዕውቀት ወጣቶችን ማነፅ** 20

እውቀት እና ክኅሎትን ማጎልበት ..... 23

**ደኅንነቱ የተጠበቀ እና የተነቃቃ የሚዲያ ምኅዳር** 23

ሥልጠናው በአሠልጣኞች አንደበት ..... 25

የመገናኛ ብዙኃን ደኅንነት እና ጥበቃ ..... 27

**የዲጂታል ዘመንን መዋጀት** 28

**የዴሞክራሲያዊነት ሒደትን መከታተል** 30

ተጨማሪ ፎቶዎች ..... 31

# ስለ ካርድ አጭር መግለጫ

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ሴንተር ፎር አድቫንስመንት ኦፍ ራይትስ ኤንድ ዴሞክራሲ /ካርድ/) ቦርድ-መር፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ 113/2011 መሠረት፣ በኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥጣን መዝገብ ቁጥር 4307፣ ሐምሌ 17፣ 2011 ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ነው። ካርድ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ተፈጥራ ማየትን ራዕይ አድርጎ ሰንቆ፣ የዴሞክራሲ መርሖዎችን በማስተጋባት ዴሞክራሲ በኢትየጵያ ብቸኛው የጫወታ ሕግ የማድረግ ተልዕኮ ይዞ እየሠራ የሚገኝ ድርጅት ነው።

ካርድ ሰብዓዊ መብቶች እና ዴሞክራሲያዊ መሠረት ያላቸው ሕዝባዊ ንቅናቄዎችን ለመገንባት የግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ሲቪል ተቋማትን የማደራጀት፣ እና የፖሊሲ መሻሻሎችን ማግባባት ሥራዎችን ይሠራል።






# የመሪ ቃላችን ፅንሰ ሐሳብ

ኢትዮጵያውያን ፈጣን እና ስልታዊ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው በርካታ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች አሏቸው። በዚህም ምክንያት የፖለቲካ ሥልጣንን በመቆጣጠር ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተመሠረቱ ብዙ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ። ይሁንና ብዙውን ጊዜ ነውጥ ሥልጣን ላይ መወጣጫ እና መሰንበቻ እንዲሁም የተፅዕኖ አድማስ ማስፋፊያ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ ፖለቲካዊ አንድምታ ያለው የነውጠኝነት ባሕል የሰው ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት፣ ለመሠረተ ልማቶች ውድመት፣ እንዲሁም ብዙኃን መሠረታዊ ፍላጎታቸው እንዳይሟሉላቸው እና ኢትዮጵያውያን ኑሯቸውን በድኅነት አዙሪት ውስጥ እንዲቀጥል አድርጓል።

የመብቶች እና ዕድገት ማዕከል (ካርድ) ውስጥ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ኢትዮጵያውያን ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ሰላማዊ እና ዘላቂ የመፍትሔ አማራጮችን ያመጣል ብለን እናምናለን። እንዲሁም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ወደ ሥምምነት የሚያደርሳቸውን ጉዞ ለመጀመር ዴሞክራሲ ብቸኛው የጨዋታው ሕግ መሆን አለበት ብለን እናምናለን።



## ዴሞክራሲን ብቸኛው የጨዋታ ሕግ ማድረግ

# መርሓ ግብሮች

ካርድ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊነትን ለመገንባት መብቶች-ተኮር የሆነ አካሔድ ይከተላል።

በዚህም መሠረት የተቀረፁ አምስት መርሓ ግብሮች አሉት።

1. CARD – የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል – CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY – CIVIC ENGAGEMENT
2. CARD – የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል – CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY – YOUTH AND WOMEN EMPOWERMENT
3. CARD – የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል – CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY – MEDIA LITERACY
4. CARD – የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል – CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY – DIGITAL RIGHTS
5. CARD – የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል – CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY – DEMOCRATIZATION INDEX



# 1. የዜግነት ተሳትፎ

ይህ መርሐ ግብር ብዝኃነት የተላበሱ የሰብዓዊ መብቶች እና ዴሞክራሲያዊ ጉዳዮች ላይ ዜጎች ተሳትፎ የሚያደርጉባቸው ተቋማት እና መድረኮች እንዲፈጠሩ ለማስቻል ያለመ ነው። ፕሮግራሙ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች እና ወጣት መሪዎች ሙያዊ እና ቁሳዊ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ በማገዝ፣ የግል ተነሳሽነታቸውን ተቋማዊ፣ እንዲሁም ኢ-መደበኛ ንቅናቄያቸውን መደበኛ እንዲያደርጉ እና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር እና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ማኅበራዊ መሠረት ለማቆም ይሠራል። በዚህ መርሐ ግብር ውስጥ ያሉት ፕሮግራሞች እና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

- መደበኛ፣ ኢ-መደበኛ፣ እንዲሁም ልማዳዊ የሆኑ ቡድኖች ንቅናቄዎቻቸውን ተቋማዊ እንዲያደርጉ የማብቃት ሥራ መሥራት
- አዳዲስ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ሰብዓዊና ቁሳዊ አቅም ግንባታ በማድረግ የተፅዕኖ አቅማቸውን ማጎልበት
- ተከታታይ በይነ-ቡድናዊ ወይም የእርስ በርስ የውይይት መድረኮችን በተለያዩ አነጋጋሪ ማኅበረፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በማመቻቸት መግባባት መፍጠር
- የግጭት መንስዔዎችን በመመርመር ለሁሉን አካታች መፍትሔ ማመቻቸት.



# 2. የወጣቶች እና ሴቶች አቅም ማጎልበት

ይህ መርሐ ግብር የብቃት ማሳደጊያ ዕድሎችን በማመቻቸት ወጣቶች እና ሴቶች በዜግነት ጉዳዮች ላይ ተሳትፏቸውን እንዲያሳድጉ ለማስቻል ያለመ ነው። መርሐ ግብሩ የወጣቶች እና ሴቶችን አቅም በማሳደግ ፍትሐዊ እና ሁሉን አካታች እንዲሁም አሳታፊ ስርዓተ ማኅበር እንዲፈጠር በዕውቀት እና ሥልጠና የታገዘ ዴሞክራሲያዊ እና የሰብዓዊ መብቶች ንቅናቄ የብዙኃን መሠረት እንዲኖረው ይሠራል። በዚህ መርሐ ግብር ሥር ያሉ ፕሮጀክቶች እና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው። .

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን እና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የሰብዓዊ መብቶች እሴቶች እና የዴሞክራሲ መርሖዎችን የሚያስተዋውቁ ሥልጠናዎች እንዲያገኙ በማድረግ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ
- የወጣቶች እና ሴቶችን አቅም በማጎልበት ዕውቀት መር ማኅበራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ የምርምር መድረኮችን መፍጠር
- አካታችነት እና ብዝኃነትን የሚያበረታቱ የሰብዓዊ መብቶች ክብረ በዓላት እና ሴሚናሮችን፣ እንዲሁም የተለያዩ መደብ አቋራጭ የንግግር መድረኮችን ማዘጋጀት
- የስርዓተ ፆታ መብቶችን እና የተገለሉ እና ተጋላጭ የማኅበረሰብ ክፍሎችን መብቶች ማሳደግ





# ፫. የሚዲያ አረዳድ ክኅሎት

ይህ መርሐ ግብር የዴሞክራሲ ባሕልን ለመገንባት የብዙኃን መገናኛዎች አቅም እና ምኅዳር እንዲጎለብት ለማስቻል ያለመ ነው። ፕሮግራሙ የሚዲያ ባለሙያዎችን እና የበይነመረብ አምደኞችን ሙያዊ ብቃት እና ሥነ ምግባር የሚያሳድጉ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን በማቅረብ፣ የሐሰተኛ መረጃዎችን በመከላከል፣ በጋዜጠኞች ማኅበራት መካከል ትብብር በመፍጠር ነጻ እና ጠንካራ የሚዲያ ማኅበረሰብ እና ምኅዳር እንዲፈጠር ይሠራል። በዚህ መርሐ ግብር ሥር ያሉ ፕሮጀክቶች እና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

- ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትና የብዙኃን መገናኛዎች ምኅዳር እንዲሻሻል ግፊት ማድረግ
- ለሙያዊ ጋዜጠኝነት መጎልበት የጋዜጠኞችን ደኅንነት እና ነጻነት መጠበቅ እና መከላከል
- በመደበኛ እና ኢመደበኛ መድረኮች የሚስተዋሉ ትርክቶችን፣ የተዛቡ መረጃዎችን፣ የጥላቻ ንግግሮችን መከታተል እና የተዋስዖ መድረኩ በሥነ ምግባር እንዲታገዝ የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት
- በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ ብዙኃን መገናኛዎች የተረጋገጠ እና ብዝኃነት ያለው የሐሳብ እና መረጃ ይዘት እንዲኖራቸው ማግባባት



# 4. የዲጂታል መብቶች

ይህ መርሓ ግብር የዲጂታል መብቶች እንዲከበሩ እና የበይነመረብ ተጠቃሚ ዜጎች ደኅንነት እንዲጠበቅ ያለመ ነው። ፕሮግራሙ የበይነመረብ ተጠቃሚ ዜጎች ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እና ደኅንነታቸው እንዲጠበቅ የአድቮኬሲ/ሙግት እና የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠናዎችን በመስጠት የዜጎችን ዲጂታል ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ይሠራል። በዚህ መርሓ ግብር ሥር ያሉ ፕሮጀክቶች እና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

- በማኅበረሰብ ክፍሎች ዘንድ ያለውን የዲጂታል ክፍፍል ለመቀነስ ነጻ እና ሁሉን አካታች የበይነመረብ ተዳራሽነት እንዲኖር ማግባባት
- ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት እና የመረጃ የማግኘት መብቶች በይነመረብ ላይ እንዲከበሩ መቆም
- የግለሰቦች የበይነመረብ ዳታ፣ የግል ምሥጢር፣ እና ደኅንነት እንዲጠበቅ ማበረታታት
- የበይነመረብ ኩባንያዎች አገራዊ እና ነባራዊ ዐውዶችን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቶችን እንዲዘረጉ ድጋፍ መስጠት



# ፭. የዴሞክራሲያዊነት ምዘና

ይህ መርሓ ግብር በኢትዮጵያ ያሉ ክልላዊ እና ፌዴራላዊ መስተዳድሮችን አሠራር በዴሞክራሲ መርሖዎች በመለካት ተከታታይ የሆነ መግለጫ በማውጣት የዴሞክራሲያሚነት ሒደት እንዲሻሻል ለማገዝ ያለመ ነው። ፕሮግራሙ በሙከራ ላይ ያለ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት ውስጥ ያሉ ክልሎችን እና የፌዴራል ከተሞችን ዓመታዊ የዴሞክራሲያዊነት ሒደት በመገምገም በየዓመቱ ውጤቱን ይፋ በማድረግ ሒደቱን መከታተል እና ሕጋዊ እና ተግባራዊ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይሠራል። ይህ መርሓ ግብር ያሉት ፕሮጀክቶች እና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

- ክልሎች እና ፌዴራላዊ አስተዳደሮችን በየዓመቱ በሚደረግ የዴሞክራሲያዊ መርሖዎች መመዘኛ እና ደረጃ አሰጣጥ ስርዓት የዴሞክራሲያዊነት ሒደትን መገምገምና አስተዳደሮች እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከራሳቸው ያለፉ ዓመታት ተሞክሮ ጋር ጤናማ ፉክክር እንዲያደርጉ ማስቻል
- በምርምር የታገዘ መረጃ የመስተዳድሮችን ጥንካሬ እና ደካማ ጎን በማደራጀት ባለድርሻ አካላት ሊሠሩባቸው የሚገባቸውን የትኩረት አቅጣጫዎች በቀላሉ እንዲለዩ ማገዝ



# ሥነ ዘዴያችን ከራዕያችን ያለው ዝምድና

ከላይ በተገለጸው ዴሞክራሲን ብቸኛው የጨዋታ ሕግ ማድረግ  በሚለው መርሓችን መሠረት፥ የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) በሰብዓዊ መብቶች እሴቶች ላይ የዴሞክራሲ ባሕል የዳበረባትን ኢትዮጵያን ለማየት ይፈልጋል። ለዚህም ወጣቱን በዳበረ ዕውቀት ላይ የተመረኮዘ እና የሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤን በማስጨበጥ እሴቶቹን ተቀብለው ሕዝባዊና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን እንዲመሩ ማድረግ አንዱ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው።

በተለይ የምንጠቀምበት ሥነ ዘዴ በተልዕኳችን ላይ እንደተገለጸው የማኅበረሰቡን ንቁ ተሳትፊነት እና በዜግነት ጉዳዮች ላይ ባለቤትነቱን ማረጋገጥ ነው። የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እና የማኅበራዊ ንቅናቄ መሪዎችን ራስ-መር እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉ ለማስቻል አቅማቸውን የማጎልበት ሥራ እንሠራለን።

የካርድ አምስት መርሓ ግብሮች የተቀረፁት ከዚህ ሥነ ዘዴ ጋር በሚጣጣም መልኩ ነው። ሁሉም ፕሮግራሞች ለተሻለ የሚዲያ እና የሲቪክ (የዜግነት ተሳትፎ) ምኅዳር ግንባታ እንዲሁም የሕግ የበላይነትን መከበር ይጥራሉ። ካርድ የሚተገብራቸው ፕሮጀክቶች ከእነዚህ የመርሓ ግብር ዘርፎች ጋር የተጣጣሙ ከመሆናቸው፣ እንዲሁም ከመርሓ ግብሩ እና የድርጅቱን ዓላማዎች እና ራዕይ ከማሳካት አንፃር በየጊዜው ይገመገማሉ።

ለራዕያችን መሳካት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ በማድረግ ያግዙን ዘንድ በሁሉም የፕሮጀክት አፈፃፀሞቻችን የፖሊሲ ማግባባት፣ የተቋማት አጋርነት እና ትብብር፣ ዕውቀት ማስጨበጥ እና ግንዛቤ ማሳደግ እንዲሁም ለዴሞክራሲያዊነት ማኅበራዊ መሠረት መጣልን እንደ መንገድ እንከተላለን።


የዲሞክራሲያዊነት
ባሕል በኢትዮጵያ
የሚዲያ ምኅዳር
የሕግ የበላይነት
የሲቪክ ምኅዳር
የሰብዓዊ
መብቶች እሴቶች
የዜግነት ተሳትፎ
የሚዲያ አረዳድ ክኅሎት
የወጣቶች እና ሴቶችን አቅም ማጎልበት
የዲጂታል መብቶች
የዲሞክራሲያዊነት ምዘና
አይሮኬሲ
አጋርነት እና ትብብር
እውቀት እና ግንዛቤ ማስጨበጥ
ለዲሞክራሲያዊነት ማኅበራዊ መሠረት መጣል

## በመንገዳችን የሚያተጉን ተስፋዎች

# የዜጎች በራሳቸው ጉዳይ ባለቤት መሆን

የዜጎች ንቁ ተሳትፎ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት መለያ ባሕሪ ነው። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ደግሞ የዜጎችን ተሳትፎዎች በማረጋገጥ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ተጫዋቾች ናቸው። ነገር ግን በኢትዮጵያ ያሉት  የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ አብዛኛዎቹ በኢትዮጵያ ዋና ከተማና መሐል አገር አዲስ አበባ የተከማቹ ናቸው። በመሆኑም፣ የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) መደበኛ እና ኢመደበኛ ሲቪክ ማኅበራትን እንዲሁም በግለሰባዊ ተነሳሽነት የተጀመሩ ተቋማት በሙያዊ እና ቁሳዊ አቅም ግንባታ በማሳደግ ጠንካራ እና በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ፍትሐዊ ተደራሽ የሆኑ፣ ዜጎችን የሚያሳትፉ መድረኮች እና ንቅናቄዎች ተፈጥረው የዴሞክራሲ ባሕላችንን በመላው ኢትዮጵያ መገንባት እንደሚቻል ያምናል።

ካርድ የዜግነት ተሳትፎ በተሰኘው መርሐ ግብራችን ሥር የዜጎች ተሳትፎን የሚያረጋግጥ ስርዓተ ሥልጠና የያዘ ፕሮጀክት የቀረፀው በዚህ አግባብ ነው ነው። የዚህ ፕሮጀክት የመጀመሪያው አምድ በክፍል ውስጥ የሚሰጡ ሰባት ርዕሰ ጉዳዮችን የሚዳስስ ተከታታይ ሥልጠና ነው። ሥልጠናው ከሰብዓዊ መብቶች መሠረታውያን ጀምሮ፣ የፕሮጀክት ዐውድ አፈፃፀም፣ የአድቮኬሲ እና ግንኙነት ርዕሰ ጉዳዮችን ጭምር ይዳስሳል። ሠልጣኞች የክፍል ውስጥ ሥልጠናዎችን ካጠናቀቁ በኋላ ለተግባራዊ ልምምድ በቡድን የዜግነት ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚላኩ ሲሆን፣ ሁለተኛውን ዙር የተግባር ልምምድ ካጠናቀቁ በኋላ አዳዲስ የሲቪል ድርጅቶች እንዲፈጥሩ የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

በዚህ ሒደት ካርድ እስካሁን ድረስ በአማራ፣ በጋምቤላ፣ በሶማሊ እና በኦሮሚያ ክልሎች አዲስ የተመሠረቱ አራት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ አስችሏል።





“ካርድ ያዘጋጀውን ሥልጠና ስወስድ በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የሦስተኛ ዓመት ተመራቂ ተማሪ ነበርኩ። ሥልጠናው በአጠቃላይ ስድስት ወር ነው የፈጀው። ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የማኔጅመንት ትምህርት ነበር የማጠናው። የወጣት አፍሪካ መሪዎች ኢኒሼቲቭ አልሙናይም ነኝ፤ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ባሉ ክበቦች - እንደ ስርዓተ ፆታ እና የፀረ-ሙስና ክበባት በንቃት ተሳትፎ አደርግ ነበር።



ምሕረት ዋለልኝ፤ የ‹ኸር ኢትዮጵያ› መሥራች እና የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ.

በካርድ የተዘጋጀውን ሥልጠና ከመውሰዴ በፊት ስለ ድርጅቶች አመራርም ይሁን ስለ ፕሮጀክት ዐውድ አፈፃፀም ምንም ዓይነት ልምድ አልነበረኝም። ሥልጠናው ስለ ሰብዓዊ መብቶች ምንነት፣ ስለ ፕሮጀክት ምክረ ሐሳቦች አጻጻፍ እና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮችን ያካተተ ነበር። ጥልቀት ያለው እና ሁሉን ዐቀፍ ሥልጠና ነበር።

የካርድ ሠራተኞች እንዲሁም አሠልጣኞቻችን በሥልጠናው አጠቃላይ ሒደት ውስጥ ቀለል ያለ አቀራረብ የነበራቸው እና በአስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ተባባሪዎች ነበሩ። ይህ ባሕሪያቸውም ሥልጠናውን በሙሉ ፍላጎት ተከታትዬ እንድጨርስ ብርታት ሆኖኛል።

‹ኸር ኢትዮጵያ›  የተሰኘውን ድርጅት ለመመሥረት የመጀመሪያ ምክረ ሐሳብ ስጽፍም ከካርድ አባላት እገዛ አግኝቻለው። ድርጅቱን በማቋቋም ሒደትና በመጀመሪያው ፕሮጀክታችን ትግበራ ላይ ከካርድ ከፍተኛ ድጋፍ አግኝተናል። የካርድ ሠራተኞች ሁልጊዜም ለእኛ ተደራሽ ነበሩ።



*በሥምምነታችን ከተቀመጡ መብቶች በላይ ለምናቀርብላቸው ጥያቄዎች ሁሉ ምላሽ ይሰጡናል። ከተመሠረትን በኋላ ባለው አንድ ዓመት ውስጥ ካርድ እንቅስቃሴያችንን ተከታትለውናል፤ የፕሮጀክት አፈፃፀማችንን ሒደት በተመለከተ ድጋፍ አድርገውልናል፤ እንዲሁም የፋይናንስ አስተዳደርን ጨምሮ ሌሎች አቅም ግንባታ ዕድሎችን ሰጥተውናል።*

*በእነዚህ እገዛዎች ምክንያት ስንመሠረት በፕሮጀክታችን ከያዝነው ተጨማሪ ተግባራትን ልናካትት ችለናል። በክልሎች ልንሰጥ ያቀድነውን ሥልጠና ሰጥተናል፤ ከመንግሥት ድርጅቶች ጋር ጥሩ ግንኙነት ፈጥረናል፤ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ትስስሮችን ፈጥረናል፤ እንዲሁም  በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዕውቅና ተሰጥቶን ባዘጋጁት የሴቶች ቀን ክብረ በዓል ላይ ለመጋበዝ በቅተናል። በጅግጅጋ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጋር አጋርነትን ፈጥረናል። ይህ እንደ ትልቅ ስኬት የምንወስደው ነው። ከጅግጅጋ ውጭም ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጋር ግንኙነት መሥርተናል። ከፕሮጀክታችን ተጠቃሚዎች፣ ሠልጣኞቻችን እና ሌሎች አጋሮቻችን ያሉበት ቦታ ድረስ ተቀራርቦ የመሥራት ልምድን ከካርድ ተምረናል። በዚህ ምክንያት ሥልጠና ለመስጠት እና ዶክመንተሪ ለመሥራት የሚያስችለንን አገልግሎት በነጻ  ማግኘት ችለናል። ስለዚህ አጋርነትን በመፍጠር ረገድ ለቀሰምነው እና ላዳበርነው ልምድ ካርድ ትልቅ ባለውለታችን ነው።  በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ፣ በዘላቂነት በክልሉ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር እና በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሴቶች መብት በሚታሰብበት ጊዜ ቅድሚያ የሚታሰብ ድርጅት ለመሆን እንመኛለን። በተጨማሪም አድማሳችንን በማስፋት አፋር ክልል ውስጥ ከሴቶች ግርዛት እና ፆታዊ ጥቃት በዘለለ ለመሥራት አቅደናል። በዋነኝነት በተጨማሪ ለመሥራት በዕቅዳችን የያዝነው በሥነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ነው።”.*

በካርድ አማካኝነት የተመሰረተው ‹ኸር ኢትዮጵያ› የተባለው አዲስ ድርጅት በጅግጅጋ ያካሄደው የስርዓተ-ፆታ ሲምፖዚየም.



# ስለ ሰላም መቆም

የካርድ "ዴሞክራሲን ብቸኛው የጨዋታው ሕግ ማድረግ" የሚለው መርሕ የትኛውም ዓይነት አለመግባባቶች በሰላማዊ እና አሳታፊ መንገድ ብቻ መፈታት እንዳለባቸው በቁርጠኝነት እንደምናምን ማሳያችን ነው። በዜግነት ተሳትፎ ፕሮግራማችን ሥር፣ የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) ሰዎች ግጭቶችን በውይይት መፍታት እንዲለማመዱ እና የጋራ መግባባትን ለመፍጠር መድረኮችን እንዲያመቻቹ የሚያግዙ የውይይት ፕሮግራሞችን ይቀርፃል። በተጨማሪም ካርድ በሁሉም ፕሮጀክቶቹ ውስጥ ግጭት አገናዛቢ መርሖዎችን ተግባራዊ በማድረግ ፕሮጀክቶቹን ያከናውናል። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ግዜው ግጭቶች የተበራከቱበት እና ለሰላም ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ የሆነበት መሆኑ ነው።




በተጨማሪም ካርድ በመላው ኢትዮጵያ የሚነሱ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ በፅናት የሚሟገት ድርጅት ነው። ከበርካታ አገር በቀል የሲቪል የማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በግጭቶች ውስጥ የሚሳተፉ ተዋናዮች ሁሉ ልዩነቶቻቸውን ለመፍታት ሰላማዊ መንገዶችን ብቻ እንዲመርጡ እና ነውጥን በአስቸኳይ እንዲያቆሙ ጥሪ ያቀርባል። በትግራይ ጦርነት ወቅት፣ ብዙ ፈተናዎች እና እንቅፋቶች ቢጋረጡበትም ቅሉ፥ ካርድ ተግዳሮቶቹን ሁሉ በመጋፈጥ ከመሰል ድርጅቶች ጋር በመቆም የሰላም ጥሪውን በተደጋጋሚ ሲያቀርብ ነበር።

# ተሟጋች ትውልድ ማፍራት

የወደፊት ተስፋን ለማረጋገጥ ወጣቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ካርድ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊነት ጉዞ በፈታኝ መንገድ የሰነበተበት ምክንያት የሰብዓዊ መብቶች እሴቶችን እና የዴሞክራሲዊነት መርሖዎችን ለማስተዋወቅ የሚደረጉ ንቅናቄዎች የኅብረተሰቡን ሰፊ ክፍል የያዘውን ወጣት እንዲሁም ለጥቃት ተጋላጭ እና ግፉዓን የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማረጋገጥ ባለመቻቻላቸው እንደሆነ ያምናል። ስለሆነም ብዙ ወጣቶችን እና ሴቶችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ወደ መድረክ ማምጣት አስፈላጊ እንደሆነ ሙሉ እምነታችን ነው።

የወጣቶች እና ሴቶችን አቅም ማጎልበት የተሰኘው ፕሮግራማችን ሴቶችን እና ወጣቶችን ብቁ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ዕድሎችንና መድረኮችን በማመቻቸት የወጣቶችን እና ሴቶችን በዜግነት ጉዳዮች የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ያለመ ነው። በዚህም፣ ካርድ ዋነኛ ዓላማው የሆነውን ለሰብዓዊ መብቶች መከበር እና ለዴሞክራሲያዊነት የሚተጋ ትውልድ በማፍራት ረገድ የበኩሉን አስተዋፅዖ ማበርከት እንደሚችል ያምናል።

በዚህ የወጣቶች እና ሴቶችን አቅም ማጎልበት ፕሮግራም ሥር ካሉት ቀዳሚ ፕሮጀክቶች አንዱ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች አዲስ ትውልድ የተሰኘ ሲሆን፥ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች መሆን የሚያስችላቸው ተከታታይ ሥልጠናዎችን የሚያገኙበት ነው።

*“አዲስ አበባ የሚገኘው አሚጎንያን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ እያለሁ ካርድ ሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ ያዘጋጀውን ተከታታይ ሥልጠና አግኝቻለሁ። በ2013 ሥልጠናውን ከወሰዱ ቀዳሚ ሠልጣኞች አንዷ ነኝ። ሥልጠናው ብቃት እንዲኖረን ያስቻለንና አበረታች የነበረ ሲሆን ሥልጠናውን እንደጨረስን በትምህርት ቤታችን ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች እሴቶችን የሚያሳድግ እና ለሴቶች መብቶች የሚታገል ክበብ መሥርተናል።*



ሶሊያና ዶጁ፤ በሰብአዊ መብቶች ፌስቲቫል ላይ። ሶሊያና መስራች የሆነችበት የአሚጎኒያ የወጣቶች መብቶች ተሟጋቾች ክበብ ከ50 በላይ አባላት ከደረሱ በኋላ በመጋቢት 2014 በፌስቲቫል አክብረዋል

*በመጀመሪያ ከካርድ በተሰጠን የሰብዓዊ መብቶች ሥልጠና ተነሳስተን 14 አባላት ያሉት እና በተማሪዎች ስለሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ የሚሰጥ የወጣት ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች የሚል ሥያሜ ያለው የትምህርት ቤት ክበብ ለማቋቋም ወሰንን። በመቀጠልም ከ9ኛ እና 12ኛ ክፍል የተውጣጡ 45 ተማሪዎችን መርጠን ከካርድ ያገኘነውን ማሠልጠኛ ሞጁል መሠረት አድርገን ሥልጠና ሰጠናቸው።*

*በክበቡ ውስጥ የኔ ድርሻ የነበረው ለተማሪዎቹ ሥልጠና መስጠት ነበር። ለተመረጡት 45 ተማሪዎች ሥልጠና ከመስጠት ባሻገርም በትምህርት ቤታችን ዋና ቅርንጫፍ ተማሪዎችን ወክዬ እሳተፍ እና በርካታ ጊዜም ንግግሮችን አደርግ ነበር። ባለሙያዎችን*

*እየጋበዝኩ ተማሪዎች በጊዜ አጠቃቀም እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ አድርጌያለሁ። ከሥልጠናው በኋላ የተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት ሲጨምር፣ የንግግር ችሎታ ሲሻሻል እና የንባብ ቡድኖች ሲስፋፉ በግልጽ ይስተዋል ነበር።*

*በመጨረሻም በትምህርት ቤታችን [አሚጎኒያን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት] የካርድ እና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ደኅንነት ማኅበር ዋና ዳይሬክተሮች እንዲሁም ወላጆቻችንን በመጋበዝ ሠልጣኞቹን ያስመረቅንበት የተሳካ ፕሮግራም አዘጋጅተናል። ትምህርት ቤታችን ይህንን ክበብ በማደራጀትን እና ውጤታማ ሥራ በመሥራታችን ለክበቡ አባላት የምስክር ወረቀት ሰጥቶናል። በተጨማም ክበቡ በዘላቂነት እንዲቀጥል ስለምንፈልግ አሁን ክበቡን እየመራን ያለነው ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ በምንገባበት ወቅት ክበቡን ለመምራት የሚችሉ ተተኪ ተማሪዎችን በአመራር ውስጥ አስገብተናል።*

*ለሁሉም ሰው መብት የሚቆም የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ለመሆን እሠራለሁ።”*

በ2013/14 ካርድ ከአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ 364 የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በዐሥር ዙር ተከታታይ እና የተሳኩ ሥልጠናዎችን ከሰጠ በኋላ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች አዲስ ትውልድ በማለት ሠይሟቸዋል። እነዚህ ሠልጣኞች በአዲስ አበባ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሰብዓዊ መብቶች ተሟጋችነት ባላቸው ፍላጎት መሠረት የተመረጡ ሲሆን በሰብዓዊ መብቶች ፅንሰ-ሐሳብ፣ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት፣ የስርዓተ ፆታ እኩልነት፣ የመሰብሰብ እና የመደራጀት ነፃነትን የተመለከቱ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች አራት ርዕሰ ጉዳዮችን ሠልጥነዋል።



ካርድ በ2014/15 ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በሐዋሳ፣ በአዳማ፣ በደብረብርሃን፣ በቢሾፍቱ፣ በድሬዳዋ እና በሐረር ከተሞች ይህንኑ ሥልጠና በመስጠት ተደራሽነቱን በክልል በሚገኙ ከተሞችም እንዲስፋፋ አድርጓል። በዚሁ ዓመት ይህንን ተከታታይ

ሥልጠና ያገኙ አጠቃላይ ተማሪዎች ቁጥር 370 ተማሪዎች ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 59.5% ያክሉ ሴት ተማሪዎች ናቸው። ካርድ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች አዲስ ትውልድ አባላት ጋር ያለውን ግንኙነት ዘላቂ ለማድረግ አሁንም እየሠራ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ኮሚሽነር ዳንኤል በቀለ (ዶ/ር) በ2015 የሰብዓዊ መብቶች ፌስቲቫል በተሰራጨ ገላጭ መጽሔት ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፥ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ የባሕላችን አካል ሆኖ የማየት ራዕይ እውን የመሆን ዕድሉ በወጣቶች ላይ የተመሠረተ እንደሆነ በአፅንዖት ገልጸዋል።

የ2015 የሰብአዊ መብቶች ፌስቲቫል ከፊል እይታ፣ ሠልጣኞች ተመርቀው ከሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ጋር በጎንዮሽ ዐውደ ርዕይ የሚተዋወቁበት ፌስቲቫል.



# በአገር በቀል ዕውቀት ወጣቶችን ማነፅ

ውርድወት የምርምር ፌሎሺፕ ሌላው የወጣቶች እና ሴቶችን አቅም ማጎልበት ፕሮግራም ሥር ያለ ፕሮጀክት ነው። ሥያሜውም የዛሬ 160 ዓመት ገደማ፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በጉራጌ ማኅበረሰብ የኖች እና ለሴቶች እኩል የትዳር ውስጥ መብቶች በመታሏ በጉራጌ ትውፊት ውስጥ የቃቄ ውርደወት እየተባለች ከምትታወስ ሴት ነው። የምርምር ፌሎሽፑ በሰብዓዊ መብቶች ርዕሰ ጉዳይ ላይ ምርምር በመሥራት ሙያቸውን ለማሳደግ ፍላጎት ላላቸው ኢትዮጵያውያን ሴቶች እና ወጣቶች የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግበት ነው። በተጨማሪም ወጣቶቹ ሙያቸውን እያሳደጉ እግረ መንገዳቸውን በሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች፣ በልማዳዊ/ትውፊታዊ ተቋማት እና በኢትዮጵያ ግፉዓን እና ለጥቃት ተጋላጭ በሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሁኔታ ላይ ምርምሮችን በማድረግ ፍትሐዊ ማኅበረሰብ ለማምጣት ሐሳባቸውን የማስተዋወቅ ዕድል ያገኛሉ።


ካርድ ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ሰባት የውርድወት የምርምር ፌሎዎችን አፍርቷል። በውርድወት የምርምር ፌሎውሺፕ፣ ካርድ ወጣቶችን በተለይም ወጣት ሴቶችን በተመራማሪነት ለማብቃት የሚያልም ሲሆን አልፎ ተርፎም ግፉዓን እና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የተመለከቱ ጉዳዮችን የሚዳስሱ፣ በማስረጃዎች ላይ የተመሠረቱ ጥናቶችን አሳትሟል።

# ከውርድወት የምርምር ፌሎዎች አንደበት




ነፀብራቅ ታመነ፤ የ2014 የውርድወት የምርምር ፌሎውሺፕ ተሳታፊ እና "የካ፤ የሲዳማ ሴቶች ተቋም እና ያልተነገረለት አቅም" ደራሲ


*"በ2014፤ በኢትዮጵያ የገጠር ሴቶች ስለ ከተሜ ሴቶች የመብቶች እንቅስቃሴ ግንዛቤ ባይኖራቸውም የራሳቸውን መብቶች የሚያስከብሩባቸው እና ማንነታቸውን የሚያስጠብቁባቸውን ትውፊታዊ ተቋማት በተመለከተ ለአንድ ዝግጅት ገለጻ ለማድረግ እየተዘጋጀሁ ነበር። በዚህ ወቅት ነው የካ ስለሚባል የሲዳማ ሴቶች መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ እና ራሳቸውን ከቤት ውስጥ ጥቃት ለመከላከል የሚጠቀሙበት ትውፊታዊ ተቋም ላውቅ የቻልኩት። ብዙ የብሔረሰቡ ወጣቶችን ሳናግር ግን ይህንን ትውፊታዊ ተቋም የማያውቁ መሆናቸውን ተረዳሁ። በዚህም ምክንያት ስለ ጉዳዩ ምርምር ለማድረግ እና የማገኘውንም መረጃ ሌሎች እንዲያውቁት ለማሰራጨት ተነሳሳሁ። በውርድወት የምርምር ፌሎውሺፕ አማካኝነት ይህንን ፍላጎቴን የሚያሳካልኝ ዕድል አገኘሁ።"*



“ከመጀመሪያዎቹ የውርድወት የምርምር ፌሎዎች አንዱ ሆኜ በመመረጤ ኩራት ይሰማኛል። የኦሮሞ ሴቶች ትውፊታዊ ተቋማት የሴቶችን መብቶች በማስከበር ረገድ ያላቸውን ሚና በተመለከተ ምርምር አድርጌያለው። ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ ክልከላዎች እና በእንቅስቃሴ ወቅት የሚያጋጥሙ የደኅንነት ስጋቶች መሰናክል ቢሆኑብኝም፣ የጀመርኩትን ምርምር ለማጠናቀቅ ችያለሁ። በምርምሬ የደረስኩባቸውን ግኝቶች በኅትመት ቅጂ ታትመው ተሰራጭተዋል። እንዲሁም በካርድ ድረ ገጽ ላይ ታትመዋል።



ሙሉቀን ካሳሁን፤ የ2012 የውርድወት የምርምር ፌሎው እና የ "ገዳ ስርዓት እና የሴቶች መብቶች" ደራሲ




ለወደፊቱ የውርድወት የምርምር ፌሎዎች የሚኖረኝ ምክር ቢኖር የጊዜ አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ትኩረት እንዲሰጡበት እና የሚኖራቸውን ጊዜ በአግባቡ እንዲጠቀሙበት የሚል ነው። የውርድወት የምርምር ፌሎውሺፕ በአፍሪካ እና በዓለም ታዋቂ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።”

# ደኅንነቱ የተጠበቀ እና
# የተነቃቃ የሚዲያ ምኅዳር

ካርድ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ ነጻነት እንዲሁም የጋዜጠኞች ደኅንነት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከበር የሚተጋ ድርጅት ነው። ለዚህም ካርድ የጋዜጠኞችን እንዲሁም የሚዲያ ባለሙያዎች የሙያ ማኅበራትን ሙያዊ ብቃታቸውን የጠበቁ ይዘቶችን የማዘጋጀት አቅማቸውን ለማጎልበትና መብቶቻቸውን ለማስከበር እንዲችሉ አቅም ግንባታ በመስጠት ተሳትፎ ሲያደርግ ነበር። .

## እውቀት እና ክኅሎትን ማኅልበት




ካርድ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በወቅታዊው የፖለቲካ ሁኔታ፣ የዲጂታል ቴክኖሎጂው ካመጣው ዕድል ጋር በተያያዘ እና በግጭቶች ሳቢያ በኢትዮጵያ ውስጥ የተስፋፋውን የሐሰተኛ መረጃዎች፣ የጥላቻ ንግግር እና ግጭት ቆስቋሽ መልዕክቶችን ስርጭት ለመከላከል ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ሲያደርግ ቆይቷል።


ካርድ ለጋዜጠኞች እና የበይነመረብ አምደኞች ሐሰተኛ መረጃዎችን የመረዳት እና የመከላከል አቅማቸውን በማሳደግ፣ የተዛቡ መረጃዎችን እና የጥላቻ ንግግሮችን ለመለየት እንዲችሉ እና እንዲከላከሉ፣ ከግጭት ቀስቃሽ ይዘቶች

እንዲቆጠቡ፣ የግጭት አገናዛቢነት ፅንሰ ሐሳብን እንዲያሰርፁ የሚያስችሉ በአገርኛ ቋንቋዎች የተዘጋጁ መማሪያዎችን አዘጋጅቷል። በዚህ ሒደት ውስጥ ካርድ ዕውቀትን በማከማቸት እና በማሳደግ ረገድ ለሚዲያ ቤተሰቦች አስተዋፅዖ ማበርከት ችሏል። ዕውቀት እና ምርምሮችን የማበልፀግ እንቅስቃሴዎች ተከታታይ በሆኑ ክትትል እና ጥናቶች የተደገፉ ናቸው። እስካሁን ድረስ ካርድ፣ በማኅበራዊ አውታሮች በሚሰራጩ ይዘቶች እና መሬት ላይ በሚነሱ ግጭቶች መካከል ስላለው ግንኙነት በየሁለት ሳምንቱ የሚወጡ ከ60 በላይ ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለባለድርሻ አካላት አሰራጭቷል።

በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ግንዛቤን ለመጨመር ካርድ በ2015 የኢትዮጵያን የሚዲያ ተቋማት እና የሰው ኃይላቸን ቆጠራ አካሔዷል። እንዲሁም በኢትዮጵያ ሚዲያዎች ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ውስጥ የግጭት አገናዛቢነት ፅንሰ ሐሳብ መካተቱን ግምገማ በማካሔድ ግጭት አገናዛቢነት የተሻለ ትኩረት እንዲሰጠው ሞዴልግጭት አገናዛቢ የአርትኦት ረቂቅ ፖሊሲ አዘጋጅቷል።

ካርድ ለጋዜጠኞች እና ለበይነመረብ አምደኞች የሚሆኑ ተከታታይ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት ከፍተኛ ብቃት አዳብሯል። ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የሐሰተኛ መረጃዎችን ለመከላከል እንዲሁም የግጭት እና የሰብዓዊ መብቶች አገናዛቢነት ፅንሰ ሐሳብን ማስተዋቅ ላይ ያተኮሩ የሕግ ማዕቀፎችን የተመለከተ ሥልጠና ሲሰጥ ቆይቷል። ከነዚህ መካከል፣ ካርድ በ2014/15 በዐሥራ ስድስት የኢትዮጵያ ከተሞች ባመቻቸው ተከታታይ ሥልጠናዎች 364 ጋዜጠኞች እና የበይነመረብ አምደኞች ተጠቃሚ ያደረገው ከኔዘርላንድስ ዓለም ዐቀፍ ሬዲዮ (RNW) እና ከአሜሪካ ኤምባሲ ጋር በመተባበር ባዘጋጀው ሥልጠና ነበር። ካርድ ተከታታይ ሥልጠናዎችን በሚሰጠበት ወቅት አሠልጣኝ በማሠልጠን የሚጀምር ሲሆን፥ ይህም በተለያዩ ርዕሰ ጉዳይ የአሠልጣኞችን እጥረት ለመቅረፍ ድርብ ግብ አለው።

# ሥልጠናው በአሠልጣኞች አንደበት



ሮኖቦት አያሌው፤ የሐቅ ማረጋገጥ ባለሙያ እና አማካሪ

*“በካርድ እና በኔዘርላንድስ ዐለም ዐቀፍ ሬዲዮ (RNW) ነሐሴ 2014 ላይ የተዘጋጀው የአሠልጣኞች ሥልጠና ላይ ተሳትፌያለሁ። ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ለጋዜጠኞች፣ ለማኅበራዊ ሚዲያ ይዘት አዘጋጆች እና ለሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሥልጠና ስሰጥ ስለነበር የአሰልጣኝነት ልምድ ነበረኝ። ነገር ግን አብዛኛው ልምዴ በግል ጥረት ያገኘሁት ብቻ ነበር። ይህ የአሠሰልጣኞች ሥልጠና እንደ አሠልጣኝ የሚያስፈልግ ክኅሎት እና መመሪያ ስላገኘሁበት ጠቃሚ ተሞክሮ ነበር።*

*የአሠልጣኞች ሥልጠና ላይ ከተማርናቸው የሐቅ መመርመሪያ እና ማጣሪያ ዘዴዎችን ብዙዎቹን አስቀድሜ ባውቃቸውም፣ በሥልጠናው የተካተቱት ሌሎች ለአሠልጣኝነት የሚጠቅሙ ዘዴዎችን በተመለከተ የተሻለ እውቀት እንዲኖረኝ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ሥልጠናው በበይነመረብ ከመሆኑ በቀር ሁሉንም ሠልጣኝ ያማከለ እና በንቃት እንዲሳተፉ የሚያደርግ አቀራረብ ነበረው። በዚህም ምክንያት ከዚህ ቀደም ሥልጠና እሰጥበት የነበረውን ‹የማስተማር› ዓይነት ዘዴ በመቀየር ሠልጣኞች ንቁ ሚና እንዲጫወቱ የሚያስችላቸውን ከሠልጣኞች ሐሳብ ተነስቼ የማሠለጥንበትን ዘዴ መከተል ጀምሬያለው። በአሠልጣኞች ሥልጠና ላይ የመሳተፍ ዕድሉን በማግኘቴ እና የፕሮጀክቱ አካል በመሆኔ ራሴን ዕድለኛ አድርጌ እቆጥራለሁ። በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ሥልጠናዎችን መስጠቴም በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ስላለው ሁኔታ ሰፋ ያለ ዕይታ እና ግንዛቤ እንዲኖረኝ አድርጎኛል። ስለ አሠልጣኞች እና ሊያውቋቸው የሚገቡ ክኅሎቶች የበለጠ ትምህርት በመውሰድ ሙያዬን እንደምቀጥል ተስፋ አደርጋለሁ።”*

*“በኢትዮጵያ የዲጂታል ሚዲያ ዕድገት ጋር በተያያዘ የተዛቡ መረጃዎች የሚያደርሱት ተፅዕኖ ከዋና ችግሮች አንዱ እየሆነ እና እንደ ጥላቻ፣ ሁከት እና በአገሪቱ ውስጥ አለመረጋጋት እንዲፈጠር አስተዋጽዖ እያደረገ ይገኛል። ካርድ ከኔዘርላንድስ ዓለም ዐቀፉ ሬዲዮ እና በአዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ በመተባበር በ2014 ግንቦት ወር ኢጋማሽ ላይ ለጋዜጠኞች እና ለማኅበራዊ ሚዲያ ይዘት አዘጋጆች በዚህ ፕሮጀክት ላይ እንዲሳተፉ የአራት ቀናት ሥልጠና ሰጥቷል።*




ተስፋዬ ወልደዮሃስ፣ አማካሪ እና አሰልጣኝ

*በዚህ ፕሮግራም ላይ የአሠልጣኞችን ሥልጠና ከወሰድኩ በኋላ በአሠልጣኝነት ለመሳተፍ ዕድሉን አግኝቻለሁ። ሥልጠናውን በወሰድኩ ወቅት ስለተለያዩ የተዛቡ መረጃ ዓይነቶች፣ እንዲሁም የተሳሳቱ መረጃዎችን ለማጣራት የሚጠቅሙ ዘዴዎችን እና አጠቃቀማቸውን ለማወቅ ዕድሉን አግኝቻለሁ። በመጨረሻም የአሠልጣኞች ሥልጠናውን ከወሰድኩ በኋላ በ11 የተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ከ200 በላይ ጋዜጠኞችን አሠልጥኛለሁ፤ ይህም ሌላ ልምድ የቀሰምኩበት እና የተማርኩበት ዕድል ነበር።”*



# የመገናኛ ብዙኃን ደኅንነት እና ጥበቃ




የተነቃቃ የመገናኛ ብዙኃን ዴሞክራሲን ለማስፈን እንደሚጠቅመው ሁሉ ደኅንነቱ የተጠበቀ የመገናኛ ብዙኃን ምኅዳርም የተነቃቃ የመገናኛ ብዙኃን እንዲኖሩ ያስችላል። ለዚህም ነው ካርድ የሚዲያውን ምኅዳር እና የባለሙያዎችን ደህንነት እና ጥበቃ ትኩረት ሰጥቶ የሚስቀሳቀሰው። ካርድ ሁሌም ጥቃት ከሚደርስባቸው ጋዜጠኞች ጎን በመቆም የበለጠ ሊያሠራ የሚችል የሚዲያ ሕግ እና ምኅዳር እንዲኖር ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ያከናውናል።

ካርድ የጋዜጠኞች ማኅበራት እንዲጠናከሩ እና የአባላቶቻቸውን ደኅንነት በሚመለከት በጥምረት እንዲሠሩ የሚያስችላቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ሲሠራ ነበር። ለጠንካራ የሚዲያ ማኅበራት መፈጠር የምናደርገው ድጋፍ ደኅንነቱ የተጠበቀ የሚዲያ ምኅዳር እንዲኖር ጋዜጠኞች ስለራሳቸው በራሳቸው ጥብቅና መቆም የሚችሉበትን አቅም ለመፍጠር ነው።

# የዲጂታል ዘመንን መዋጀት




መጪው ዘመን የዲጂታል ነው። ካርድ ኢትዮጵያ የዲጂታል ዘመን የሚያመጣላትን ትሩፋት በአዎንታ መቀበል እንዳለባት እና ከቴክኖሎጂው ጋር ተያይዘው የሚከተሉትን ተግዳሮቶች ለመቋቋም የሚያስችል አቅም ማዳበር እንደሚኖርባት ያምናል። የዲጂታል ቴክኖሎጂ ወደ ዴሞክራሲያዊነት የማሸጋገር አቅሙም ከፍ ያለ ነው። ስለዚህም ካርድ መሬት ላይ የሚከበሩ የሰብዓዊ መብቶች በይነመረብ ላይም እንዲከበሩ እና ጥበቃ እንዲደረግላቸው ይሟገታል።

ካርድ በይነመረብ ላይ የሚንቀሳቀሱ ወይም በበይነመረብ ተሳታፊ ዜጎች የግል ምሥጢራቸው እንዳይጓደል እና ከአደገኛ ንግግሮች  እንዲጠበቁ የተሟጋችነት ሥራ ይሠራል።  ካርድ የዲጂታል መብቶችን ለማስጠበቅ የሚሠራቸው ሥራዎች ሁለት ገጽታዎች አሉት። በአንድ በኩል በይነመረብ በፍትሐዊነት እና በዘላቂነት ተዳራሽ

እንዲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የዲጂታል ዜጎችን ደኅንነት ለማስጠበቅ የሚረዳ ሕጋዊ እና የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲኖር መሥራት ነው። ካርድ የበይነመረብ ተደራሽነት እንዲስፋፋ በሚሠራው የተሟጋችነት ሥራ የዓለም ዐቀፉ #KeepItOn ጥምረት አባል ሆኗል። በዚህም የበይነመረብ መታገድን ወይም የሶሻል ሚዲያ መዘጋትን በመቃወም ያለማቋረጥ ይሟገታል። ካርድ የሚያደርገውን የተሟጋችነት ሥራ በበይነረመብ ግንኙነት መቆራረጥ ላይ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ የበይነረመብ አግልግሎት ተደራሽ የሆነው አንድ አራተኛ ለሚሆን ማኅበረሰብ ብቻ ከመሆኑ አንፃር ፍትሐዊ በሆነ መልኩ በመላው ኢትዮጵያ ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግም ጭምር ይሟገታል።

በተጨማሪም ካርድ #KeepItSafe የሚለውን ሀሽታግ በመጠቀም የማኅበራዊ ሚዲያዎች ዘመቻን በመጠቀም የዲጂታል ዜጎችን ደኅንነት በመንግሥት፣ በማኅበራዊ አውታሮች እና በሌሎች ዘንድ የተጠበቁ እንዲሆኑ ይሟገታል። ካርድ በ#KeepItSafe ዘመቻው ኢትዮጵያ ከሌሎች ሕጎች በተጨማሪ አጠቃላይ የመረጃ ጥበቃ ሕግ እንድታፀድቅ እና ተግባራዊ እንድታረግ ምክረ ሐሳብ አቅርቧል።



# የዴሞክራሲያዊነት ሒደትን መከታተል

ዴሞክራሲ መዳረሻ አይለም። ይልቁንም ለተወሰነ ጊዜ የብዙኃንን ይሁንታ ያገኘ መንግሥት ዜጎችን የሚያስተዳድርበት እና በቁጥር አናሳ የሆኑትን ደግሞ የሙብት ጥበቃ የሚሰጥበት ሒደት ነው። ዴሞክራሲ ከስርዓትና እና ኅብረተሰቦች ሁለንተናዊ ዕድገት ጋር ቀጣይነት ባለው መልኩ እየዳበረ የሚሔድ ስርዓት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊነት የሚጠበቀውን ያህል እመርታ አላሳየም። ለዚያም ነው በሁሉም የአስተዳደር ክፍሎች ውስጥ ዕድገቱን እና/ወይም ዝግመቱን መታዘብ አስፈላጊ የሆነው። ካርድ የዴሞክራሲያዊነት ሒደትን የመከታተል ሥራውን እውን ለማድረግ በፌደራል ስርዓቱ ውስጥ የሚገኙ የክልል መንግሥታት በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እና አፈፃፀማቸው ያሉበትን የዴሞክራሲያዊነት ደረጃ የሚገመገሙበትን የዴሞክራሲያዊነት ምዘና መሥፈርት ቀርጿል።

ይህ ፕሮግራም በሙከራ ደረጃ ላይ ቢሆንም በምን መልኩ መተግበር እንዳለበት ዝግጅቱ ተጠናቋል። ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ለመገንባት ያሉ እመርታዎችን ወይም ክፍተቶችን በየዓመቱ ለመገምገም እና ደረጃ ለመስጠት ካርድ የሚጠቀማቸው ስድስት መለኪያ መሥፈርቶች እያንዳንዳቸው አምስት ጠቋሚዎች አሏቸው።

በእነዚህ 30 ጠቋሚዎች መሠረት በሙቶዎች የሚቆጠሩ ባለሙያዎች የእያንዳንዱን ክልል አፈፃፀም በመገምገም ጥንካሬያቸውንና ድክመቶቻቸውን በማየት ከሌሎች አቻ ክልሎች ጋር በማነፃፀር ደረጃ በመስጠት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ እንዲሔዱ ዕድል ይሰጣቸዋል።



## የዴሞክራሲ ሂደት

- የግል ነጻነቶች
- ምርጫ እና ፖለቲካዊ ብዝኃነት
- ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ መብቶች
- መልካም አስተዳደር
- የኅዳጣን እና ግፉዓኖች ጥበቃ
- ቁጥጥር እና ሚዛን

ካርድ ለዴሞክራሲያዊነት ምዘና የሚጠቀማቸው ስድስቱ መስፈርቶች

# ተጨማሪ ፎቶዎች








CARD

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY

MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF THE GAME!

## ለበለጠ መረጃ


ኢሜል: info@cardeth.org
ሶሻል ሚዲያ: @CardEthiopia
ድረ ገፅ: www.cardeth.org
ስልክ: +251 116 671 657

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ


ድረ ገፃችንን ይጎብኙ